**እንደ WIC ተሳታፊ ያሉኝ መብቶች፦**

- WIC ላይ የመግቢያ ህጎች ዘር፣ ቀለም፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ዕድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት ወይም ፆታ ሳይለዩ ለሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ናቸው።
- የWIC ዓላማ ስለ አመጋገብ፣ ጡት ማጥባት እና ጤናማ ምግቦች መረጃን መስጠት እና ሊያስፈልጉኝ ከሚችሉ ሌሎች የጤና ወይም የማህበረሰብ አገልግሎቶች ጋር እንድገናኝ ማድረግ ነው። በእነዚህ አገልግሎቶች ውስጥ እንድሳተፍ እበረታታለሁ።
- ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለመደገፍ የአመጋገብ ግቦችን ለማዘጋጀት የWIC የጤና ባለሙያዎች ከእኔ ጋር ይተባበራሉ።
- ወደ ሌላ ግዛት የምሄድ ከሆነ፣ ለWIC እነግራቸው እና የWIC አገልግሎቴ እዚያም እንዲቀጥል ከእኔ ጋር የምወስዳቸው የማስተላለፊያ ወረቀቶች ይሰጡኛል።
- የ WIC ሠራተኛ WIC ላይ መሳተፍ እንደማልችል ከነገረኝ እና እኔም በዚህ ካልተስማማሁ፣ ፍትሃዊ ችሎት እንዲደረግልኝ መጠየቅ እችላለሁ። ለአካባቢዬ WIC ቢሮ ለመጻፍ ወይም ለመደወል ብቁ መሆኔን የሚገልጽ ደብዳቤ ከደረሰኝ በኋላ 60 ቀናት አሉኝ።

**እንደ WIC ተሳታፊ ያሉብኝ ኃላፊነቶች፦**

- ከአንድ በላይ የWIC ፕሮግራም ውስጥ (በግዛቱ ውስጥ ወይም ከግዛቱ ውጪ) መሳተፍ ህገወጥ ሲሆን ከፕሮግራሙ መውጣትን ያስከትልብኛል።
- በቤተሰቤ ውስጥ ላሉ የWIC አመልካቾች የWIC የጤና ምርመራን እፈቅዳለሁ። የWIC የጤና ምርመራ የጤና እና የአመጋገብ ጥያቄዎችን መመለስ፣ ቁመትን፣ ክብደትን መለካት እና የደም ማነስ ምርመራን ያካትታል። ይህም WIC ለቤተሰቤ ፍላጎት ምላሽ ሰጪ የሆኑ ጥቅማጥቅሞችን እንዲያቀርብ ይረዳል።
- በቀጠሮዎቼ እመጣለሁ ወይም ቀጠሮዬ ላይ መገኘት ካልቻልኩ አስቀድሜ እደውላለሁ።
- እንደ የመገኛ አድራሻዬ፣ የስም ለውጦች እንዲሁም በእኔ እንክብካቤ ስር ያሉ የWIC አገልግሎቶችን ለሚቀበሉ ሕጻናት የአሳዳጊ ለውጦች የመሳሰሉት፣ ሊከሰቱ የሚችሉ ማንኛቸውም ጉልህ ለውጦችን ለ WIC አሳውቃለሁ።
- የWIC ሠራተኞችን፣ የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ሠራተኞችን እና ንብረትን በትህትና እና በአክብሮት እይዛለሁ። እኔ፣ ወይም ማንኛቸውም ተወካዮቼ የWICን ሠራተኛ፣ ሌላ የWIC ደንበኛን ወይም የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ሠራተኛን በቃላት በመሳደብ፣ በማስፈራራት ወይም በአካል በመጉዳት የWIC የምግብ ጥቅማጥቅሞችን ልናጣ እንደምችል እረዳለሁ።
- በተሰጠኝ የ eWIC ካርድ የምገዛው በ WIC የምግብ ጥቅማጥቅሞች ዝርዝር ውስጥ የተዘረዘሩትን የተፈቀዱ ምግቦችን ብቻ ነው።
- የWIC ምግቦችን የምጠቀመው በፕሮግራሙ ላይ ላለ ሰው(ዎች) ብቻ ነው። እነዚህ የWIC ምግቦች የሚቀርቡት የዚያን ሰው የአመጋገብ ደህንነት ለማሳደግ እና ለመደገፍ እንዲሁም የተመከሩትን ጠቃሚ ንጥረ ነገሮች ወይም ምግቦችን ማሟላት ላይ ለመርዳት መሆኑን ተረድቻለሁ።
- ለእኔ የተሰጠኝን ምግብ/ፎርሙላ ወይም ጥቅማጥቅም ለገበያ አላቀርብም፣ አልሸጥም፣ አላስተላልፍም ወይም አልለውጥም፣ ወይም ለገበያ ለማቅረብ፣ ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም ለመለወጥ አልሞክርም። ለእኔ የተሰጠኝን ምግብ/ፎርሙላ ወይም ጥቅማጥቅም ሌላ ሰው ለሽያጭ እንዲያቀርብ፣ እንዲሸጥ፣ እንዲያስተላልፍ ወይም እንዲለውጥ አልፈቅድም።
- WIC ከሚሰጣቸው ነገሮች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ፣ የ WIC ባልሆነ ገንዘብ የገዛኋቸውና ለሽያጭ ለማቅረብ ወይም ለሰዎች ለመስጠት ያሰብኳቸውን የምግብ ወይም ፎርሙላ የሶስት ወር የሱቅ ደረሰኞችን አስቀምጣለሁ። ይህም በእኔ WIC ገንዘቦች ያልተገዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንድችል ነው።

**እንደ WIC ተሳታፊነቴ የሚከተሉትን እረዳለሁ፡-**

- የማረጋገጫ ጊዜው ሲያበቃ እንደገና ማመልከት እና ለፕሮግራሙ ብቁነት እንደገና መገምገም አለብኝ
- WIC ተጨማሪ ፕሮግራም በመሆኑ በአንድ ወር ውስጥ የሚፈለገውን ሙሉ ምግብ ወይም ፎርሙላ አያቀርብም።
- ለአራት ተከታታይ ወራት የምግብ ጥቅማጥቅሞች ካልተሰጡኝ ከፕሮግራሙ እወጣለሁ።
- Department of Health and Human Services (HHS፣ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ) የWIC መረጃዎቼ ለተወሰኑ የጤና እና የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲጋሩ ሊፈቅድ ይችላል። እነዚህ፣ ለፕሮግራሞቻቸው ብቁ መሆኔን ለመወሰን፤ ስለ እነዚያ ፕሮግራሞች መረጃ ሊሰጡኝ እና የማመልከቻውን ሂደት ቀለል ለማድረግ፤ ቀድሞውኑ በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ተመዝግቤ ከሆነ ጤንነቴን፣ ትምህርቴን ወይም ደህንነቴን ለማሻሻል፤ እንዲሁም የእኔ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ይህንን መረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ይህ መረጃ በ WIC ወኪል ድርጅቶች እና የህዝብ ድርጅቶች ለWIC ፕሮግራም ብቁ የሆኑ ሰዎችን በሚያገለግሉ ፕሮግራሞቻቸው አስተዳደር ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላል። HHS እንደአስፈላጊነቱ ወይም በፌደራል ወይም በግዛት ህግ የተፈቀደውን የWIC መረጃዬን መጋራት ሊፈቅድ እንደሚችል ተረድቻለሁ። በWIC ፖሊሲ "የተሳታፊ መረጃ ምስጢራዊነት" ላይ እንደሚታየው የWIC መረጃዬ የሚጋራላቸውን የHHS ፕሮግራሞች ዝርዝር መጠየቅ እችላለሁ።

በፕሮግራሙ ስር ስለሚኖሩኝ መብቶች እና ግዴታዎች ምክር ተሰጥቶኛል። እኔ እስከማውቀው ድረስ ለብቁነቴ መወሰኛ ያቀረብኩት መረጃ ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ። ይህ የማረጋገጫ ቅጽ የሚቀርበው የፌዴራል እርዳታን ከማግኘት ጋር በተያያዘ ነው። የፕሮግራሙ ባለስልጣናት በዚህ ቅጽ ላይ ያለውን መረጃ ማረጋገጥ ይችላሉ። ሆን ብዬ ሀሰት ወይም አሳሳች ቃል መስጠት ወይም ሆን ብዬ የተሳሳተ መረጃ ማቅረብ፣ መደበቅ ወይም መረጃን መከልከል የተሰጠኝን የምግብ ጥቅማጥቅሞችን ለግዛቱ ወኪል ድርጅት በጥሬ ገንዘብ ሊያስከፍለኝ እና በግዛት እና በፌደራል ህግ መሰረት የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ክስ ሊያስቀርብብኝ እንደሚችል ተረድቻለሁ።

ዛሬ የተረጋገጠው የWIC ተሳታፊ(ዎች) ስም፡- ______________________________________________

______________________________________________________የተሳታፊ/ወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ_______

ቀን፡-____________________________________________________

በፌዴራል የሲቪል መብቶች ህግ እና U.S. Department of Agriculture (USDA, በዩኤስ የግብርና መምሪያ) የሲቪል መብቶች ደንቦች እና ፖሊሲዎች መሰረት ይህ ተቋም ዘር፣ ቀለም፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ፆታ (የፆታ ማንነት እና ፆታዊ ዝንባሌን ጨምሮ)፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ዕድሜን መሰረት አድርጎ መድልዎ ከማድረግ፣ ወይም ቀደም ሲል በተደረገ የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ ላይ የበቀል እርምጃ ከመውሰድ የተከለከለ ነው።

የፕሮግራሙ መረጃ ከእንግሊዝኛ ውጪ በሌሎች ቋንቋዎች ሊቀርብ ይችላል። ስለፕሮግራሙ መረጃ አማራጭ የመገናኛ ዘዴ የሚያስፈልጋቸው አካል ጉዳተኞች (ለምሳሌ ብሬይል፣ ትልቅ ህትመት፣ የድምጽ ቅጂ፣ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ) ፕሮግራሙን የሚያስተዳድር ኃላፊነት ያለበትን ግዛት ወይም የአካባቢ ኤጀንሲን ወይም የUSDA TARGET ማእከልን በ (202)720-2600 (ድምፅ እና TTY) ማነጋገር አለባቸው። ወይም USDAን በፌዴራል የግንኙነት አገልግሎት በኩል በ (800) 877-8339 ያግኙ።

የፕሮግራም መድሎ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ቅሬታ አቅራቢው በ: https://www.usda.gov/sites/default/files/documents/ad-3027.pdf ላይ፣ ከየትኛውም የ USDA ቢሮ፣ በ

(866)632-9992 በመደወል ወይም ለ USDA በሚላክ ደብዳቤ በመጻፍ የሚገኘውን የ USDA Program Discrimination Complaint Form (የ USDA ፕሮግራም የአድልዎ ቅሬታ ቅጽ) የሆነውን AD-3027 ቅጽ መሙላት አለበት። ደብዳቤው የአቤቱታ አቅራቢውን ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የተባለውን መድሎአዊ ድርጊት በተመለከተ በበቂ ሁኔታ ለሲቪል መብቶች ረዳት ፀሀፊ (ASCR) ስለ ሲቪል መብቶች ጥሰቱ ዓይነት እና ቀን ማስረዳት የሚችል የጽሁፍ መግለጫ መያዝ አለበት። የተሞላው AD-3027 ቅጽ ወይም ደብዳቤ በሚከተለው መንገድ ለ USDA መቅረብ አለበት፡-

(1) በደብዳቤ፡-U.S. Department of Agriculture Office of the Assistant Secretary for Civil Rights
1400 Independence Avenue, SW Washington, D.C. 20250-9410፤ ወይም
(2) ፋክስ፡- (833)256-1665 ወይም (202)690-7442፤ ወይም
(3) ኢሜል፡- program.intake@usda.gov

ይህ ተቋም እኩል ዕድል አቅራቢ ነው።